# መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የዚህ ጥናት ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለማወቅ እገዛ ያደርጋል፤እንዲሁም እግዚአብሔርን በማወቅ ለማደግ ይረዳል።

መጽሐፍ ቅዱስ በ66 መጽሐፍት የተዋቀረ ነው።እነዚህ መጽሐፍት በምዕራፍ እንዲሁም ምዕራፎቹ በቁጥር የተከፈሉ ናቸው።ከዘፍጥረት ጀምሮ በዮሐንስ ራዕይ ይጠናቀቃል።።።እያንዳንዱን ምዕራፍ አንብባቸው፤በመቀጠልም ለእያንዳንዱ ምዕራፍ ዋናውን ርዕስ፤ታሪክ ወይም የእያንዳንዱን ምዕራፍ ዋና ነጥብን የያዘ ርዕሰ ጉዳይ ዝርዝር አዘጋጅ።(ማስታወሻ: ምናልባት ከአንድ በላይ ርዕስ፤ታሪክ ወይም ነጥብ ሊኖረው ይችላል፤ነገር ግን አስፈላጊ ነው የምትለውን አንድ ብቻ ጻፍ) ከታች የተሰጠውን ምሳሌ በሚገባ ተመልከት።

ከርዕሰ ጉዳዩም በተጨማሪ፤ዋናውን ርዕስ፤ታሪክ ወይም የእያንዳንዱ ምዕራፍ ዋና ነጥብ ውስጥ ያገኘኸውን እውነት ከህይወትህ ጋር በማዛመደ ጻፍ።በመቀጠልም ይህ መሰረታዊ እውነት በህይወትህ እንዴት እንደሚሰራ ጻፍ።

በቀን ቢያንስ ሦስት ምዕራፎችን ለማንበብ ሞክር።ዋናውን ርዕስ፤ታሪክ ወይም የእያንዳንዱን ምዕራፍ ዋና ነጥብ አስራ አምስት ጊዜ በማንበብ አስታውስ።(ማስታወሻ: መሰረታዊውን እውነት ማስታወስ ወይም በህይወትህ ላይ እንዴት መተግበር እንዳለብህ ማሰብ አይገባህም) የእያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ርዕሰ ጉዳዮች በየዕለቱ ከምታነበው ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ጋር በማዋሃድ በአዕምሮህ አምስት ጊዜ ማሰላሰል ትችላለህ።

የመጽሐፉን ሀሳብ አንብበህ፤ርዕሰጉዳዩን በሚገባ አውጥተህ እና አሰላስለህ እንደጨረስህ እንደሚከተለው ጻፈው፤

ሀ. የመጽሐፉ ዓላማ
ለ. የመጽሐፉ አጠቃላይ መልዕክት

መጽሐፉን አጥንተህ ከጨረስህ በኋላ አንድ ሰው የሰራኸውን ስራ እንዲገመግምልህ እና ያጠናኸውን ጥናት እንዲመዝንልህ አዘጋጅ።

## የምሳሌ ጥናት

ርዕሰ ጉዳይ
የጥናት ማስታወሻ

**ዘፍጥረት**

**ምዕራፍ**: 1

**ዋና ርዕስ፤ታሪክ ወይም ነጥብ**: እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ

**መሰረታዊ እውነት**: እግዚአብሔር የሁሉም ፍጥረታት ፈጣሪ ነው

**ልንማረው የሚገባ ዋና ነጥብ**: እግዚአብሔር ፈጣሪዬ ነው ለእሱም ልኖር ይገባኛል